በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኦክቶበር 21-31 እና ከኖቬምበር 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ


ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ........ - 2 -

ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 3 -

ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 3 -

ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 4 -

ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 4 -

ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ.- 5 -

ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 6 -

ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........ - 6 -

ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 8 -

ካርታ 7 ኢ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ........ - 8 -

ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........ - 8 -

ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 9 -

ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 9 -

ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸው ጋር በተያያዘ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩትን የሀገሪቱ አከባቢዎችን ጨምሮ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ወቅት ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የሲዳማ አካባቢዎች ዝናብ ያገኙ ቢሆንም፤ የደቡብ ሶማሌ አካባቢዎች ግን አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም የዝናቡ ሥርጭት በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ ኢትዮጵያ አከባቢዎች ላይ ከመስፋፋቱም ባሻገር በአንዳንድ አካባቢዎችም በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ላይ በመነሳት በ24 ሰዓት ውስጥ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች መካከል በአርጆ 32.6፣ በፓዌ 40.6፣ በጅማ 42.2፣ በቦሬ 57.0፣ በቻግኒ 32.6፣ በኢጃጂ 44.2፣ በላሬ 42.0፣ በወራቤ 38.0 እንዲሁም በሳዉላ 53.0 ይጠቀሳሉ፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ9 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.6-57.0 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በፓዌ፣ በጅማ፣ በቦሬ፣ በኢጃጂ እንዲሁም በላሬ ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የሊበንና የዳዋ ዞኖች፤ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች እንዲሁም የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች ላይ ከ11-123 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከሶማሌ የነጎብ፣ የጃረር የቆራሄ፣ የሸበል፣ የዶሎ እና የአፍዴር ዞኖች ላይ ከ5-10 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በደቡብ፣ መካከለኛው፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል የማሂ፣ ፈንቲ፣ ቅልበቲ፣ አውሲ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የሊበንና የዳዋ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው አስር ቀናት በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላላጠናቀቁ እንዲሁም ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው የመኸር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በአንጻሩ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና የሲዳማ አካባቢዎች መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኙ ቢሆንም የደቡብ ሶማሌ አካባቢ ግን በጥቂት ቦታ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ተመዝግቧል። ይህም ሁኔታ በተለይም በደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆንና በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት አዎንታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው አዋሽ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ እንዲሁም በታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በታችኛው አዋሽ ኪስ ቦታዎች መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ ለሆኑ ተፋሰሶች የውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል አዎንታዊ ሚና እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ የላይኛው ተከዜ፣ መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ዋቤሸበሌ፣ የታችኛው አዋሽ፣ የታችኛው አባይ ኪስ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች እና የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናብ ቀጣይነት ይኖረዋል (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም በፀሃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመሳት በአሶሳ እና በማኦኮሞ ልዩ ወረዳ፣ በምዕራብ፣ በምስራቅና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ዳዉሮ፣ ማጅንግ ዞን፣ በጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ደቡብ ኦሞ፣ በኣሊ፣ በአማሮ እና በጌዲኦ እንዲሁም በሲዳማ ክልል አከባቢዎች ላይ በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ ባስኬቶ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን፣ ቆራሂ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን እና ሸበል ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ ባሉት አከባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡


በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከአማራ ክልል ምዕራብ፤ ሰሜንና ማዕከላዊ ጎንደር፤ ምስራቅ፤ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፤አዊ ዞኖች እና ባህርዳር ዙሪያ፤በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ፣የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፤ ማሂ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31, 2024
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ይኖራቸዋል (ካርታ 8)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ይኖራል(ካርታ 8)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Total Rainfall (mm) 1-10,Nov 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አስራ አንድ ቀናት የሚኖረው እርጥበት በተለይም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ወራት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለተተከሉ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ እና በከተሞች አካባቢ የሚጠበቀው እርጥበት በከተማ ግብርና ለሚለሙ አትክልቶች በቂ የውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል። በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አቅርቦት መሻሻልም ሆነ መጠነኛ የበጋ ወቅት ሰብል ለሚያመርቱ እንደ ቦረናና ጉጂ ለመሳሰሉ አካባቢዎች የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር በመሆኑ ማህበረሰቡ ይህንን ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በአንጻሩ ግን የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ በሰሜንና በደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የትግራይ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ በአዲስ አበባ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ሊኖር የሚችለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ በመሳሰሉ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ ለመሰብሰብ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ በመካከለኛው እና በታችኛው አባይ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞጊቤ፣ በስምጥሸለቆ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ እና በዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። ስለሆነም የሚኖረው የእርጥበት ሁኔታ ለገፀ ምድር የውኃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ የታችኛው ተከዜ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እንዲሁም የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም ቆላማና ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት የማሰባሰብ እና በአግባቡ የማከማቸት ተግባራትን በማከናወን ለቀጣይ ደረቅ የበጋ ወራት ሊገጥም የሚችለውን የውኃ እጥረት ለመቋቋም የሚያስችል ስራ መስራት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ አፍር ደናክል፣ የላይኛው ተከዜ እና አባይ ተፋሰሶች ላይ በደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et